# አባወራ

ወንደላጤ አይደለሁ
እጮኛ ፈላጊ
አፍላ አፍቃሪ አይደለሁ
ጅንን ተውረግራጊ፧
አልፏል እንደጥላ
ቆሞቀርነቴ
በትዳር ከለላ
ተከትቷል ስጋቴ።
ቀርቷል መሳቀቄ
በራዬን ደብቄ
ሽበቴን መንጭቄ
ቦርጬን አስጨንቄ
ከዕድሜ ትንቅንቄ።

በእግዜር ፊት መሃላ
ፈቅዳኛለች ሚስቴ
ዕጣዬን ተካፍላ
ማዕድህ ማዕዴ ብላ
ገብታለች ከቤቴ፧
ላትሄድ እኔን ትታ
ትዳሯን ላትፈታ
ባምር ብንገላታ
ባሸንፍ ብረታ
ብወፍር ብከሳ
ብወድቅ ብነሳ
ባስታውስ ብረሳ
ባንኳርፍ ብፈሳ።

## ብዙ ተባዙ

የእናትነት ዕጣ፣ ያባትነት ውርሱን
የፍጥረትን ምስጢር፣ የቤተሰብ ቅርሱን
የትውልድ አደራ፣ የብዙ ተባዙን፤
ለአዕምሮህ ሳይሆን ባሻው ለሚከንፈው
ለልቦናሽ ሳይሆን ስርአት ለሚገድፈው
ለፈቃድህ ሳይሆን እብደት ለሚለክፈው
ለህሊናሽ ሳይሆን ዓለም ለሚያጎድፈው፤
ሰጠው ለሽፍደትህ ጦር ለማይመልሰው
ለመግነጢስ ገላሽ ጾም ለሚያስፈርሰው
ጻፈው በገበናሽ በጉያሽ ትኩሳት
በማትሟገተው የጭንህ ዲን እሳት፤
በሰጣችሁ ርስት በወጉ እንድትረቡ
በሴስ አቆራኝቶ በወሲብ ቀለቡ
ምድርን በሰው ሞላት በኪነጥበቡ።

These poems are from "Embilta", a poetry book in Amharic by Fasil Yitbarek
This book is available for sale from www.amazon.com
(search under Fasil Yitbarek)